# ቀንዴን አሳያለሁ ብሎ ወያኔ ቀንዱን ተመታ

ባለፉት ዓመታት ወያኔ ሲዘጋጅበት የቆየ ጉዳይ ነው-- በባዕድ ሀገር ያለውን ሁኔታ መቆጣጠ ርና የበላይነትን ማስፈን። ባለፈው ሐሙስ በዋሽንግተን ዲሲ በወያኔ አደራጅነት የተሞከረ ው ሰልፍ የዚሁ ዝግጅት መጠናቀቂያና ይፋ መውጫ፤ መጀነኒያና መፎከሪያ ይሆናል ተብሎ ነበር። ግን በሚያሳዝን ሁኔታ ከሽፏል።

ወያኔ ባለፉት ዓመታት በርካታ አባላቱን ስደተኛ እያስመሰለ ወደ አሜሪካና አውሮጳ መላኩ ከዚህ በፊት ተጋልጧል። ብዙ ሚሊዮን ብር አፍሶም በባዕድ ሀገሮች ቅጥረኞቹን አሰማርቷል። ተቃዋሚ ሀይሎችና መሪዎቻቸውን ነጋ ጠባ የሚሰድቡና የሚያጠቁ ቅጥረኞቹ ን አሰማርቷል። በየኤምባሲው ከየብሄረሰቡ የመጡ ቅጥረኞቹንም አምጥቶ እነዚህም በውጭ ነዋሪውን ኢትዮጵያዊ በብሄረሰብ ደረጃ እየቀረቡ ለመደለልና ንብረት በሀገር ቤት ያለውንም ለማስፈራራትና ለማስገበር ሲጥሩ ቆይተዋል። ለምሳሌ ሙሉጌታ የተባለው የወያኔ ተቀጣ ሪ በዋሺንግተን የጉራጌ ብሄረሰብ ተወላጆችን ለመቅረብና ለወያኔ ለማስገበር የሚያደርገውን ጥረት መጥቀስ ይቻላል። ወያኔ ዋና ትኩረቱን የሰጠው ደግሞ ዜጎችን በሚያሰባስቡ የሀይማ ኖተ ተቋሞች በመሆኑ ቅጥረኞቹን በመጠቀም የሀይማኖት ተቋሞችን መቆጣጠር ወይም መከፋፈልና ማፈራረስ ዋናው ተልዕኮው ሆኖ ቆይቷል። በቅርቡም ህጋዊ ሲኖዱን ሊከፋፍል ና ሊያሰግድ ያደረገውን ጥረትና ከዚህም ተባባሪ ደላላ የሆኑትን ከሀዲ ግለሰቦች ማየቱ ብቻ ይበቃል። በየድረ ገፁና ፓልቶኩ የወያኔ ግልፅና ድብቅ ቅጥረኞች ጫጫታም ሌላ ምስክር ነው።

ወያኔ ያለፈውን ሐሙስ ሰልፍ የጠራው ቀንዱን ለማሳየትና እነሆ በዓይናችሁ ስር ተደራጅ ቼ የበላይነትን ያዝኩ ብሎ ለመፎከር ነበር። በአላሙዲ እርዳታ ተሰላፊዎችን የመጓጓዣና የሆቴልም እከፍላላሁ ብሎ ቢጮህም ለዚህ ሰልፉ ያገኛቸው በቁጥር በጣም ትንሽ መሆናቸ ው ታይቷል። ይህም ሰልፍና ዝግጅቱ ወያኔ ዛሬም ድረስ የሚመካው በታሪክ አተላዎችና ወንጀለኞች እንጂ በሀቀኛ ሀገር ወዳዶች ላይ ሊሆን አለመቻሉንም አጋልጧል። ለምሳሌ ዋነኛው የዚህ ሰልፍ አዘጋጅ ትህትናና ይሉኝታ የለሹ ወያኔ ሲቪሊቲ ብሎ በሚጠራው ፓልቶክ ክፍል ውስጥ አስተዳዳሪ ነኝ ባዩ ራሱን አባ መላ ብሎ የሚጠራው ግለሰብ ነው። በአባ መላ ስም በስተጀርባ የተደበቀው ወያኔ ለስልጣን ሲበቃ ለወያኔ ሊያገለገል ተነስቶ ሕዝብ ግን በውንጀለኛናት ከሶ ሲያስጨንቀው በወያኔ ትብብር ስደት ወጥቶ የነበረው ብርሃኑ ዳምጤ ነው። ብርሃኑ ዳምጤ በመርካቶ አካባቢ ብርሀኑ ደቡር በሚለም ይታወቅ የነበረ ሲሆን በከፍተኛ 6 ቀበሌ 04 ነዋሪ እንደነበር ይህን አረመኔ የሚያውቁት ሁሉ ያስታ ውሳሉ፡

ብርሃኑ ደቡር ለደርግ እጁን ሰጥቶ በካድሬነት ሲሰራ የቆየ ሲሆን በቀይ ሽብሩ በቀጥታ ተሳታፊ በመሆን፤ በመጠቆምና በማጋለጥ በትንሹ ለ 32 የኢሕአፓ ደጋፊዎችና አባላት ህይወት መጥፋት ተጠያቂ የሆነ ወንጀለኛ ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ ካስገደላቸው ውስጥ ሲሳይ ተቀባን፤ እንቆ ስላሴ ደበበን፤ ከበደ ፀጋዬና ሺመልስን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ደርግም በአርሻ ሚኒሲቴር በተጠሪነት ሾሞትና ወደ ቼኮስላቫኪያም ለትምህርት ልኮት እንደነበር ይታወቃል፡፡ ዛሬ በአሀዮ ከተማ ነዋሪ ነኝ የሚለው ይህ ወንጀለኛ ለወያኔ በማደር አሁንም ሕዝብን እያደማ ያለ ነው፡፡ የወያኔን የዋሺንግተን ስልፍ ካዘጋጁት ከሀዲዎች ውስጥ ይህ ብርሃኑ ዳምጤ ወይም አባ መላ የተባለው ዋነኛው መሆኑ የወያኔን ሰው ማጣትና ክስረትም የሚጠቁም ነው፡ ለዚህም ነው ቀንዴን ላሳይ ያለው ወያኔ ቀንዱን የተመታው፡፡ አልሞት ባይ ተጋዳዩ ወያኔ  ይህን ሙከራውን ወደ አውሮጳ ከተሞችም ለማምጣት መነሳቱ አይቀር ምና በዚያ ያሉ ዜጎችም ቀንዱን ሊመቱት መዘጋጀት አለባቸው ሲሉ ታዛቢዎች ይጠቁማሉ ፡፡ ከወያኔ ጋር እየተባባሩ ያሉትንም የቀድሞ አገዛዝ ወንጀለኞችና ሽብርተኞችንም ማጋለጥ  አስፈላጊ መሆኑን ሁኔታው አሳይቷልም ተብሏል፡፡ የኢትዮጵያን ሕዝብ ትግል ለማፈን በወ ያኔና በሼክ አላሙዲ መሀል የተመሰረተው  አንድነትንም በተመለከተ ታጋይ ክፍሎችና ሕዝብም በአጠቃላይ ተገቢውን ግንዛቤ ወስዶ ሊያኖካክተው መወሰን አለበትም የሚሉ ብዙዎች ናቸው፡፡